# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 359 መጋቢት 19 2007 ገጽ 1


በጎንደር የሚታየውን የአልገዛም ባይነት ትንቅንቅ በሌሎች ክልሎችም በማቀጣጠል፤ በደብረወርቅ የታየውን የመምህራን የስራ ማቆም አድማ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋት፤ እንደ ድምፃችን ይሰማ ሁሉ ተቃውሞን ወደ እንቢተኝነት በማሸጋ ገር ...... ወዘተ የነፃነታችንን ቀን ለማቅረብ መከፈል የሚገባውን መከፈል ይገባናል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ኢትዮጵያ የአባይ ግድብ ግንባታን በየደረጃው የሚቆጣጠረውን ስምምነት ፈረመች

ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ በጋራ የፈረሙት አዲሱ ስምምነት ኢትዮጵያ በግድቡ ላይ በሙሉ ነጻነት የምትሰራውን ስራ እንደሚገድብ ከአረብኛ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው ሰነድ አመልክቷል።

ሰነዱ ኢትዮጵያ ግድቡን ለመገንባት በምታደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴና በየትኛውም የግንባታ ደረጃ ላይ አለማቀፉ አጥኝ ቡድን ለሚሰጠው አስተያየት ተገዢ በመሆን እንድትተገብር ይገልጻል። አጥኝ ኮሚቴው የግድቡ ግንባታ የግብጽንና ሱዳንን የውሃ ድርሻ መጠን ይቀንሳል ወይም በግብጽና ሱዳን አካባቢያዊ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያመጣል የሚል ድምደማ ላይ ከደረሰ ካሳ እስከመክፈል የሚያደርስ ግዴታም መጣሉ ተመልክቷል።

አጥኚ ቡድኑ የመጨረሻውን የጥናት ውጤት ይፋ ካደረገ በሁዋላ ሶስቱም አገራት እንደሚቀበሉት የተስማሙ ሲሆን፣ ምናልባት አጥኝ ቡድኑ ግድቡ በግብጽና ሱዳን ላይ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ያስከትላል ብሎ ቢወስን ኢትዮጵያ የግድቡን ቅርጽ እስከመቀየር ልትደርስ ትችላለች።

ኢትዮጵያ የምትገነባው ግድብ፣ ከግብጽና ሱዳን የውሃ ማጠራቀሚያዎችን የሚጎዳ ከሆነም ኢትዮጵያ አገራቱን ፈጥና የማሳወቅና ለውጥ ማድረግ እንደሚኖርባትም ስምምነቱ ይገልጻል።

የስምምነቱ አብዛኛው ክፍል ኢትዮጵያ ስለምትፈጽማቸው ግዴታዎች ትኩረት ያደረገ ነው። ግብጽና ሱዳን ለአባይ ወንዝ የሚያበረክቱት የውሃ ድርሻ ካለመኖሩ አንጻር ስምምነቱ በዋነኝነት ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ያላትን መብት የሚገድብ ብቻ ሳይሆን፣ የአባይ ግድብ ግንባታ እጣ ፋንታን ከኢትዮጵያ እጅ አውጥቶ በአለማቀፍ አጥኚዎች እጅ እንዲሆን የሚያደርገው ነው በሚል ትችት እየቀረበበት ነው።

ይሁን እንጅ ሶስቱም አገራት ስምምነቱን በማወደስ ለተግባራዊነቱ እንደሚሰሩ አስታውቀዋል።

## ከግብፅና ከሱዳን ጋር የሚደረገው ስምምነት የታላቁ ህዳሴ ግድብን መጠን ያስቀንሳል መባሉን ኢትዮጵያ አስተባበለች

የግብፅ ፕሬዚዳንት በኢትዮጵያ ጉብኝታቸው በፓርላማ ንግግር ያደርጋሉ።

የግብፅ የውኃና መስኖ ሚኒስትር ሆሳም አልሞጋሃዚ የኢትዮጵያ፣ የግብፅና የሱዳን የውኃ ሚኒስትሮች የመግባቢያ ሰነድ፣ ኢትዮጵያ የታላቁ ህዳሴ ግድብን ውኃ የመያዝ አቅም እንድትቀንስ ያደርጋል ማለታቸውን የኢትዮጵያ አቻቸው አጣጣሉት።

በቅርቡ የሚቀጠር አማካሪ ድርጅት የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ በግብፅና በሱዳን ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ካረጋገጠ፣ ሦስቱ አገሮች ሰሞኑን በደረሱበት የፖለቲካ መግባባት መሠረት ኢትዮጵያ የግድቡን ውኃ የመያዝ አቅም እንድትቀንስ ትገደዳለች ሲሉ የግብፅ ሚኒስትር ለአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን መናገራቸው ተሰምቶ ነበር።

የግብፅ የውኃና መስኖ ሚኒስትር እየጠቀሱ የነበረው ስምምነት ሰሞኑን የኢትዮጵያ፣ የግብፅና የሱዳን የውኃ ሚኒስትሮች በካርቱም ተገናኝተው የመግባቢያ ስምምነት ያዳረጉበትን የፖለቲካ ሰነድ ነው።

ይህ ሰነድ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረቀቀ መሆኑን ለማወቅ ቢቻልም፣ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የወሰን ተሻጋሪ ሀብቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሩ አምባሳደር ኢብራሒም ኢድሪስ በጉዳዩ ላይ ተጠይቀው መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

የግብፅ የውኃና መስኖ ሚኒስትርም .... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ኢህዴድ በሐረርጌ በጨለንቆ ከተማ ያስገነባው የሰማዕታት ሐውልት የፌዴራል ከፍተኛ ባለስልጣናት ባልተገኙበት መመረቁን ምንጮች ጠቆሙ

በቅዳሜው የሐውልት ምረቃው ላይ ያልተገኙት ጠ/ሚኒስትሩ፣ በማግስቱ በጅማ ከተማ በተካሄደው የስታዲየም ሰልፍ ላይ ተገኝተው ኦህዴድን የሚያወድስ ንግግር ቢያደርጉም እርሳቸውም ሆኑ የህወሃት ባለስልጣናት በሃውልቱ ምርቃት ላይ አልተገኙም።

የህወሃት ከፍተኛ አዛዦች በሐውልት ምረቃው ላይ ያልተገኙት "ኦህዴድን የፈጠርነው እኛ ነን" ከሚለው የህወሃቶች ትምክህት ወይም ኦህዴድ ሰማዕታት አሉኝ በማለት የሚናገረውን ላለመቀበልና ዕውቅና ላለመስጠት ሊሆን እንደሚችል ምንጮች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

የሐውልት ምረቃው በቴሌቭዥንና በሬዲዮ ጭምር በዕለቱ ሽፋን ሳይሰጠው ቀርቶ ሰኞ በትንሽ የዜና ሽፋን እንዲያገኝ መደረጉን የህወሃት ባለስልጣኖችን አለመደሰት ያሳያል ሲሉ አስተያየታቸውን አክለዋል።

በትግራይና በአማራ ክልሎች የሰማእታት ሃውልቶች ሲመረቁ የህወሃት ከፍተኛ ባለስልጣናት ተገኝተው መልእክቶችን አስተላልፈው ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ኦህዴድ ለአመታት የተጓተተውን የባህል ማዕከል ረቡዕ ለማስመረቅ አቅዶአል። .... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የፌደራል ፖሊሶች በግምገማ ተወጥረዋል

ምንጮች እንደገለጹት በአዲስ አበባ በተወሰኑ ክፍሎች የሚገኙ የፌደራል ፖሊሶች ተቃዋሚዎችን ይደግፋሉ በሚል መነሻ ጠንካራ ግምገማ እየተካሄደባቸው ነው።

የፌደራል ፖሊሶች ፌስ ቡክ እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ በተለይ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ይገናኛሉ በሚል የእጅ ስልካቸውን ተነጥቀው ፍተሻ ተደርጎባቸዋል። ለኢሳት የደረሰው መረጃ እንደሚያመለክተው እስካሁን በተካሄደው ፍተሻ ቁጥራቸው እስከ 5 የሚደርስ የፌደራል ፖሊስ አባላት ከግንቦት7 እና ኦነግ ጋር በተያያዘ መታሰራቸው ታውቋል። በሁለት የፌደራል ፖሊሶች የሞባይል ስልኮች ላይ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ፎቶ ተገኝቶባቸዋል በሚል መታሰራቸውን ምንጮች አክለው ገልጸዋል።

ምንጮች እንደሚሉት የአሁኑ ግምገማ 12 የፌደራል ፖሊሶች በተለያዩ ጊዜያት መሳሪያዎቻቸውን ይዘው መጥፋታቸውን ተከትሎ የተካሄደ ነው።

የፌደራል ፖሊስ አባላት ያለባቸው የስራ ጫናና የሚከፈላቸው ገንዘብ አለመመጣጠን፣ ምንም የትምህርት ደረጃ የሌላቸው ነባር የህወሃት ታጋዮች በተራው የፌደራል ፖሊስ አባል ላይ የሚያደርሱት ጫናና በየጊዜው የሚደረገው አስቸጋሪ ግምገማ ስርአቱን እየተው እንዲሄዱ እንደሚያስገድዳቸው ምንጮች ይገልጻሉ። አብዛኞቹ የፌደራል ፖሊስ አባላት አዛዦች ነባር የህወሃት ታጋዮች ሲሆኑ፣ የሌሎች ብሄር የፖሊስ አባላትን እንደሚንቁና እንደሚያገሉዋቸው የፖሊስ ምንጮች ይገልጻሉ።

## በአቶ ሌንጮ ለታ የሚመራው የኦዴግ ልዑካን መንግሥት ሊያነጋግረው ባለመቻሉ መመለሱን ገለጸ

"አዲስ አበባ ገብተው እንደነበር አላውቅም" አቶ ሽመልስ ከማል

ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የተቋረጠውን ድርድር ለማስጀመር መጋቢት 9 ቀን 2007 ዓ.ም. አዲስ አበባ እንደገባ የሚገልጸው በቀድሞው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ሊቀመንበር የሚመራው፣ የአሁኑ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) ልዑካን ቡድን ከመንግሥት ወገን የሚያነጋግረው በማጣቱ ወደ ካናዳ መመለሱን ገለጸ።

የኦዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፣ ከመንግሥትና ከገዥው ፓርቲ ኃላፊዎች ጋር በስልክ ከመነጋገር ባለፈ በአካል መገናኘት ባለመቻሉ ማዘኑን ገልጿል። ነገር ግን ወደ ተነሳበት ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ከመዳዝ ተስፋ እንደማያስቆርጠው አስገንዝቧል።

በተለያዩ የማኅበራዊ ድረ ገጾችና የተለያዩ ጦማሮች .... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ጉዞአችን ወደ ነፃነት ነው!! መዳረሻችንም የነፃነት አደባባይ ብቻ ነው!!

አለማችን አንባገነን ስታስተናግድ ወያኔ የመጀመሪያው አይደለም። ዘረኛንም እንዲሁ ........ እኛም ስለነፃነት ብለን ለትግል ስንነሳ የመጀመሪያዎቹ አይደለንም ...... አለማችን እንደየዘመኑና እንደ የወቅቱ አንባገነኖች ያለ የሌለ የመሳሪያና ወታደራዊ ሀይላቸውን በመጠቀም ህዝብን በፍርሀት አሸማቀውና ረግጠው ለመግዛት ሲውተረተሩ በተደጋጋሚ ታይተዋል። በዚያው ልክ ህዝባዊ ሀይልና መመከት ተስኗቸው ሲንኮታኮቱ በተደጋጋሚ የታየ ወደፊትም አናባገነኖች እስከተከሰቱ ድረስ በህዝባዊ ሀይል ተጠራርገው መቀመቅ ሲወርዱ መታየቱ አይቀሬ ነው። ህዝብ የወደደውን አስተዳዳሪ እንጂ ረግጦ ሊገዛው የሚፈልገውና አንባገነን ተቀብሎ አያውቅም፤ ዛሬም አልተቀበለም፤ ነገም አይቀበልም። ይህን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚና በጉልህ የሚታይ ግዙፍ እውነት መቼም ተቀብለውና ከታሪክ ተምረው ስለማያውቁ አሳፋሪው ውድቀታቸው በተደጋጋሚ ሲታይ አለ።

ሀገራችን የአለማችን አካል እንደመሆኗ አንባገነኖች ተፈራርቀውባታል። አንባገነኖችም በህዝባዊ ሀይል ተጠራርገውባ ታል። ከደቡብ አፍሪካ ቀጥሎ ትልቅ ወታደራዊ ሀይል የነበረው የትናንቱ ደርግ እንደ እንቧይ ካብ ሲናድ ተመልክተናል። አንባገነኖችመናገር እንጂ መስማት የማ ችሉ፤ ማየት እንጂ ማስተዋል የተሳናቸው በመሆናቸው እነሆ ዛሬም የወያኔ ዘረኛው ቡድን ህዝባ ላነሳው የነፃነትና የፍትህ ጥያቄ ያለ የሌለውን ወታደራዊ ሀይል በጠራራ ጸሀይ በማሰለፍ መቼውንም ያልተቻለ ውን ህዝብን በሀይል አሸማቆ ለመግዛት መከራውን ሲያይ ይስተዋላል። ለዚህም ነው ..... ከሌላው የሀገራችን ክልሎች ከፍ ባለ ሁኔታ የህዝባዊ እንቢተኝነት እየታየ ባለበት ጎንደርና አካባቢው በሰራዊት ማጥለቅለቅ የተያያዘው።

ለሚነሱ ህዝባዊ ተቃውሞዎችና ህዝባዊ የመብት ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሾች እስር፤ አፈናና ግድያ ከሆነ ህዝባዊ እንቢተኝነትን ማስከተሉ አይቀሬ ነው። በእስር፤ በአፈናና በግድያ እንዲሁም በሰራዊት ሀይል ህዝብን በማሸማቀቅ በስልጣን መቆየት የሚቻል ቢሆን ደርግም ከቤተ-መንግስት ባልወጣ፤ ወያኔም ዛሬ ከቤተ-መንግስቱ ባልተንፈለለሰ ነበር። ይህ ደግሞ ሊያስተምር በተገባ ነበር።

እስከ ዛሬ የትኛውም አንባገነን ስርአት በሚተማመንበት የወታደራዊ ሀይል አማካይነት የመንኮታኮቻቸውን ሰአት በአንድ ሰኮንድ ማዘግየት የቻለ እንደሌለ ሁሉ ወያኔም ያለ የሌለውን ወታደራዊ ሀይል ሲያርመሰምስ ውሎ ቢያድር ውድ ቀቱን በአንድ ሰኮንድ ማዘግየት እንደማይችል በተለይ እንቢ ለነፃነቴ፤ እንቢ ለሀገሬ... ብለን ለትግል የተነሳን ሀይሎች በመረ ዳት፤ ይበልጡኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተቀጣጠለ ያለውን ህዝባዊ እንቢተኝነት ይበልጥ እያሰፋን የጀመርነውን የነፃነት ጉዞ ከነፃነታችን አደባባይ ለማድረስ ሌት ተቀን የመስራት ሀላፊነታችናና መወጣት ይገባናል።

በጎንደር የሚታየውን የአልገዛም ባይነት ትንቅንቅ በሌሎች ክልሎችም በማቀጣጠል፤ በደብረወርቅ የታየውን የመምህራን የስራ ማቆም አድማ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋት፤ እንደ ድምፃችን ይሰማ ሁሉ ተቃውሞን ወደ እንቢተኝነት በማሸጋ ገር ...... ወዘተ የነፃነታችንን ቀን ለማቅረብ መከፈል የሚገባውን መክፈል ይገባናል።

በደርግ ላይ የተነሳው እንቢተኝነት እያየለ ሲመጣ ያሰለፈው ሰራዊት ወያኔን አጅቦ የደርግን ቀብር እንደቆፈረለት ሁሉ ዛሬም በወያኔ ላይ እየተቀጣጠለ የሚገኘው ህዝባዊ እንቢተኝነት እየጠነከረ በመጣ ቁጥር የደረደረው ሰራዊት የወያኔን ቀብር ቆፋሪ ከመሆኑ እንደማኢመለስ ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን በመማር ነፃነታችንን ለማስከበር የጀመርነውን የእንቢተኝነት ትግል በ መ ላው የሀገራችን ክፍሎች በማስፋትና በማቀጣጠል አይቀሬውን የወያኔ ቀብር ለማቅረብ በአንድነት የነፃነት ጉዞውን እንቀ ላቀል። የጀመርነው የነፃነት ጉዞ መቆሚያው የነፃነታችን አደባባይ መሆኑን በተግባር ከምናሳይበት ወቅት ላይ እንገኛለንና በአንድነት እንነሳ!!!!!

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!!**

---

## ከግብፅና ከሱዳን ጋር የሚደረገው ስምምነት የታላቁ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ስምምነቱ ኢትዮጵያ የግድቡን መጠን እንድትቀንስ ሊያስገድዳት የሚችል ነው ካሉ በኋላ፣ የግድቡን የግንባታ ሒደት ሦስቱ አገሮች በጋራ እንዲቆጣጠሩት ያስችላልም ብለዋል። ይሁን እንጂ ዝርዝር የፖለቲካ ስምምነቱ በሦስቱም መንግሥታት እስካሁን ይፋ አልሆነም።

በዚህ ጉዳይ ላይ የአሜሪካ ድምፅ አማርኛ አገልግሎት ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ የውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስትሩ አቶ ዓለማየሁ ተገኑ የግብፅ አቻቸውን መግለጫ አጣጥለውታል።

"መስማማት የምንችለው በተወያየንበት ጉዳይ ነው።" ያሉት አቶ ዓለማየሁ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ በሱዳን በተወያዩበት ወቅት በግድቡ ውኃ የመያዝ መጠን ላይ እንዳልተነጋገሩና ሰነዱም ላይ አለመካተቱን አስታውቀዋል።

ይህንን የግድቡ መጠን ይቀንስ የሚል መከራከሪያ ግብፆች በተደጋጋሚ አንስተው የኢትዮጵያ መንግሥት አቋም በግልጽ ተነግሯቸዋል ብለዋል። የስምምነቱ ዋና ዋና ነጥቦች ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን፣ ጉልህ ጉዳት አለማድረስንና የመሳሰሉ አጠቃላይ መርሆዎችን የሚመለከቱ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

በንዑስ ተፋሰስ ሥር ያሉ አገሮች የራሳቸውን ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉና በምሥራቅ የተፋሰሱ አገሮች መካከል የተደረሰው ስምምነትም ይህንን የሚያጠናክር ነው ብለዋል።

በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ሦስቱ አገሮች በዚህ ሳምንት የፖለቲካ ስምምነቱን በሱዳን ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በዚህ ሳምንትም የግብፅ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ በኢትዮጵያ ከመጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የሦስት ቀናት የሥራ ጉብኝት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ፓርላማ በመገኘትም ለሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ንግግር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ማቲያስና ከኢትዮጵያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ አባላት ጋር ተገናኝተው ይመክራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

---

## ኢህዴድ በሐረርጌ በጨለንቆ ከተማ ያስገነባው የሰማዕታት ሐውልት ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

አዲስ አበባ ስታዲየም አካባቢ የተገነባው የኦሮሞ የባህል ማዕከል መጠናቀቅ ከነበረበት ከሶስት ዓመት በላይ መዘግየቱን ምንጮች ይገልጻሉ

የኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ከሚያገኛቸው ጥቅሞች መካከል ት/ቤቶችን መገንባት፣ የባህል ማዕከላትን ማቋቋም የሚሉት ጉዳዮች የሚገኙበት ሲሆን በአዲስአበባ በአስሩም ክፍለከተሞች አንድ የኦሮሞ ት/ቤት ለመገንባት ተይዞ የነበረው ዕቅድ ባልታወቀ ምክንያት ሊተገበር አልቻለም። ኦህዴድ በህገመንግስቱ ላይ የሰፈሩ ጥቅሞችን ሆን ብሎ እንዳይፈጸሙ ያደናቅፋል በሚል በራሱ አባላት ጭምር ጠንካራ ትችቶች እንደሚደርስበት ይታወቃል።
በሐረር፣ በጅማ፣ በነቀምቴ፣ በሻሸመኔ፣ በአምቦ፣ በአዳማ ከተሞች በመቶ ሚሊየን ብር ወጪ በማፍሰስ በኣሉን ሲያከብር የቆየው ኦህዴድ ፣ የፊታችን ሐሙስ በሸራተን እና በሚሌኒየም አዳራሽ በሚያካሂደው ፌሽታ በኣሉን ይፈጽማል። ሕወሃትም 40ኛ ዓመት በአሉን ከመንግስት ካዝና በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በማውጣት በፌሽታ አክብሯል።

---

# ዘመናዊ ባሪያ ፍንገላ በኢትዮጵያ

ነፃነት ዘለቀ (ከአዲስ አበባ) **ክፍል 1**

በታሪክ ትምህርት የሚወሳ "የባሪያ ፈንጋይ ሥርዓት" የሚባል ማኅበረሰብኣዊ ዕድገት የወለደው ጥንታዊ ሥርዓት ነበር። ያ ሥርዓት በወቅቱ በሰው ዘር መካከል ትልቅ የልዩነት ቋጥኝ ፈጥሮ አንዱን ጌታ ሌላውን ሎሌና ከዚያም አልፎ የጊዜ ማሳለፊያና የመዝናኛ ዕቃ በማድረግ የማይፋቅ ጠባሳ አስቀምጦ ያለፈ ሥርዓት ነው(ሰውን ከአንበሣና ከነብር እያታገሉ በሰው ስቃይ የሚደሰቱ መኳንንትና መሣፍንት ነበሩ)። ለዚህ ሲያስቡት እንኳን ለሚዘገንን የታሪክ ስብራት አሜሪካ ጎያው ምሥክር ናት - ምንም እንኳ ነገሮች በተወሰነ መልክና ባልተጠበቀ መንገድ ቅርጻቸውን ለውጠው የጉዳቱ ሰለባዎች ለይስሙላም ቢሆን አሁን አሁን መንበረ ሥልጣን የጨበጡ ቢመስሉም የጓዳ ጎድጓዳው ታሪክ አሁንም ብዙ የተለወጠ አይመስልም - በጥቁርና በነጭ የሚታየው የዘር ልዩነት አሁንም ድረስ አልጠፋምና። አፍሪካውያንና ካሪቢያውያን በተለይም ጋናንና ቤኒንን የመሳሰሉ የባሪያ ንግድ ይጧጧፍባቸው የነበሩ ሀገሮችም ቋሚ ምሥክሮች ናቸው። የእነኩንታኩንቴ ታሪክ መቼም ቢሆን በጎያውነት ይቆያል። በኢትዮጵያም እነግንደበረትና እነሰሜን ሸዋ፣ እነቦንጋም ይመስክሩ። ቋንጃ መቁረጥ፣ የሰውን ልጅ ዛፍ ሥር ኮልኩሎ በወፈረና በከሳ፣ በዕድሜ በገፋና ባልገፋ፣ ባጠረና በረዘመ፣ ከብት ይመስል ጥርሱን በሸረፈና ባልሸረፈ … እየተባለ የሰው ልጅ እንደእንስሳና እንደአሞሌ ጨው በገንዘብ ወይም በዓይነት ይሸጥ ይለወጥ ነበር። ያ እንግዲህ ዱሮ ነው። አልፏል። መልኩን ቀይሮ በኢትዮጵያችን ሊያውም ሰላምን፣ ፍትህን፣ ነፃነትን፣ እኩልነትንና ዴሞክራሲን ከአንደበቱ በማይነጥለው የሕወሓት መንግሥት በዘመናዊ መልኩ አሁንና ዛሬ እውን ሲሆን ግን ምን እንላለን? "ጭቆናና መድሎ አስመርሮኝ ሕዝቤን ነፃ ላወጣ ለትግል በረሃ ወጣሁ" የሚለው ሕወሓት ጥንት የሞተን የባሪያ ፈንጋይ ሥርዓት ነፍስ ዘርቶበትና አቀንቃኝ ሆኖ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቅ ሲል በተለይ የድርጊቱ ሰለባዎች ምን ይዋጠን? አሣዛኝ ድርጊት በሀገራችን እየተፈጸመ ነው። እመለስበታለሁ።

በዚህን ሰሞን "ኑሮ በአዲስ አበባ" በሚል ርዕስ አንድ መጣጥፍ ማቅረቤን ተከትሎ ከወትሮው ለዬት ባለና እኔንም ባስገረመኝ ሁኔታ ብዙ አንባቢያን ልባዊ እርካታቸውን በመግለጽ በግል አድራሻየ መይለውልኛል። ለሁሉም በወቅቱ መልስ ሰጥቻለሁ። ግን በዚህ አጋጣሚ ለሁሉም በሁሉም አንባቢያንና በድረገፆቻችን ስም በድጋሚ ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። ከውድ ጊዜያቸው ተሻምተው ያን ብሶት-ወለድ ረጂም መጣጥፍ በማንበባቸውና በኑሯችን ከምር አዝነውም ያን የመሰለ ነፍስና ሥጋን የሚያለመልም የሞራል ድጋፍ ከዚያቹው ዕንቁ ጊዜያቸው ሰውተው በመላካቸው አሁንም ምሥጋናየ ድንበር የለውም - ጫት ቤቶችንና መጠጥ ቤቶችን ስታዘብ በኛ ሀገር በኮንቴይነር አሸገን ወደዓለም የጊዜ ገበያ ኢክስፖርት ልናደርገው የምንችለው "ጊዜ" በብዛት እንዳለን ብገነዘብም በውጭ ሀገራት ለሰላምታ እንኳን ጊዜ እጅግ ውድና ብርቅ እንደሆነ እሰማለሁ - ለዚህም ይመስላል ሰዎች በእግር እየተጓዙ በተመሳሳይ ቅጽበት ስልክ የሚያናገሩት፣ ምግብ የሚመገቡት፣ ጽሑፍ የሚያነቡትና… በአካባቢ የሚከናወንን ነገር የሚቃኙት። አንዲት ደቂቃ ወርቅ ናት። እንደውነቱ ከሆነ ጽሑፍ መጻፍ ከጀመርኩ ጊዜ አንስቶ ጽሑፌን በማንበብ ይህን ያህል በሀገሩ ጉዳይ ልቡ የተነካ አንባቢ ገጥሞኝ አያውቅም። በኔ የጋዜጠኝነት ዕውቀት የአንድ ሰው አጸፋ(feedback) በመቶ ሰው ይመነዘራል። ስለዚህም እስካሁኒቷ ቅጽበት ብቻ በጎ አስተያየታቸውን የላኩልኝ 15 ሰዎች 1500 ሰዎችን እንደሚወክሉና አጻጻፌንና መልእክቴን ክፉኛ ነቅፎ የወቀሰኝ አንድ ሰው ደግሞ በሌላኛው ጎራ 100 ሰዎችን እንደሚወክል በወያኔያዊ ቋንቋ ግንዛቤ ወስጃለሁ። የዚህኛውን ሰው አስተያየት ለፍርድ እንዲያመች በመጨረሻው ላይ እንዳለ አስቀምጠዋለሁ። የሌሎችን ግን ሙያ በልብ ነውና በኔው ይቅር። ግን ግን አይዞን፤ እንደጨለመብን አንቀርም። የተበተነው የሚሰበሰብበት፣ የተራብ በልቶ የሚጠግብበት፣ ጠግቦ የሚዘል አደብ የሚገዛበት፣ ፍትህ ርትዕ የሚሠፍንበት፣ ፍቅርና መተማመን የሚናኝበት፣ የእህል በረከት የሚበዛበት፣ … እውነተኛ የመኖሪያ ድባብ በሀገራችን በጣም በቅርቡ ይፈጠራል። እንዲህ ይታየኛል። ገደሉን ጨርሰን ጫፍ የደረስንም ይመስለኛል። መመኪያየ ግን ኢትዮጵያን ፈጥሮ የማይረሣት አምላከ ኢትዮጵያ ወአምላከ ኩሉ ዓለም እንጂ ሰው አይደለም።ተስፋችን እሱ ነው።

ድረ ገፆችን በሚመለከት ሁሉንም ማመስገን እፈልጋለሁ። እነሱ ባይኖሩ የነፃነት ትግላችን በብዙ ማይሎች ወደኋላ ይቀር ነበር። ችግራችን እንዲሰማ፣ የሌላው ዓለም ሕዝብም እንዲያውቅልን፣ የነፃነት አርበኞች እንዲጠራሩና እንዲወያዩ … በማድረግ ረገድ እየከፈሉ ያሉት ከፍተኛ መስዋዕትነት በታሪክም በፈጣሪም ዘንድ ትልቅ ዋጋ የሚያሰጣቸው ነው። አምላክ ይጠብቃቸው።

ይህን ስልም ከነህፀፃቸው ነው። ዓለማችን ምሉዕ በኩልሄ አይደለችም። ፍጹምነት የለም። ማንም በምንም ዓይነት መለኪያ ፍጹም አይደለም። ከዚህ ፍጹምነትን ከመሻት አኳያ ማናችንም ብንሆን በየሥራችን እንዳንታበይ ወንድማዊ ምክሬን መሰንዘር እወዳለሁ። ያጠፋን ሳይመስለኝ የምናጠፋበት ጊዜ ብዙ ነው። ዐውቀን የምናጠፋበት ጊዜም እንደዚሁ አለ። ቂም የምንቋጥር፣ በቡድን ስሜት በመገፋት በግል ያልበደሉንን የምናሣዝን፣ መቻቻልን የማናውቅ፣ በዱሮ በሬ የምናርስና ከረሜላ እንደከለከሉት ሕጻን በቀላሉ የምናርኮፍ፣ ወዘተ. አለን። ሰዎች እንደመሆናችን አመንነውም ካድነውም እንሳሳታለን። እኔ በበኩሌ እንደዚህ ነኝ። እሳሳታለሁ፤ በስህተቴም እጸጸታለሁ። ይቅር በሉኝ ብዬም የበደልኳቸውን ሰዎች ከልብ በመነጨ ስሜት እለምናለሁ። እንዲያ ስንሆን ይመስለኛል የሰው ልጅን የዕድገት መሰላል ወደላይ የምንወጣው። እንዲህ ካልሆን ታጥቦ ጭቃ እንሆናለን፤ ንግግራችንና ተግባራችንም ለዬቅል እንደሆነ ይቀራል። በንግግር ብዙዎቻችን እጅግ መሳጭ ነን - በምግባር ግን ያን ያህል አንሆንም። በጸጸትና በንስሃ፣ በመደማመጥና በመግባባት በተመሠረተ ይቅር መባባል መንፈሣዊ ፈውስን ካላገኘን በመጎሻመጥና በመገፈታተር፣ በትዕቢትና በትምክህት የትም አንደርስም - ምናልባት የነዚህ ነገሮች አባትና የክፋት አበጋዝ ወደሆነው የዲያብሎስ ቤተ መንግሥት ልናመራ እንችል ይሆናል - ያ ደግሞ ብዙ ልፋትና ድካም የለበትም። ቂምንና በደልን ሠርዞ (ልብ በል - ረስቶ አላልኩም! የተረሣ ይታወሳልና።) በአንተ ትብስ በአንቺ ትብሽ በአዲስ መልክ ፍቅርንና መዋደድን መመሥረት ግን ከባድ ከባድ ቢመስልምና ቢሆንም ይቻላል - ባሕርያዊ እልኸኝነትንና ዕብሪትን ማሸነፍ ከጦርነቶች ሁሉ ከባዱ ይመስለኛል፤ ጽጌረዳ ታምራለች፤ ይቅር ባይነትም ሃሤትን የሚያረብብ ዕፁብ ድንቅ ነገር ነው - ወደአምላክም ያስጠጋል፤ ሁለቱም ግን እሾሃማ ናቸው - በቀላል አይገኙም፤ ጽጌረዳዋ እጅን የሚወጋ ጦረኛ እሾህ፣ ይቅርባይነትም ስሜትን የሚፈታተን መግነጢሳዊ ኃይል አላቸው። እስከማውቀው ድረስ ትዕቢትና እልኸኝነት ማንንም አዋጥተው አያውቅም። ስሙን ቄስ ይጥራውና ያን የአዳምና የሔዋንን ቀንደኛ ጠላትም ወደታችኛው ዓለም(the nether-world) ከገነት አውጥቶ ያሽቀነጠረው ይሄው ትዕቢት ነው።

ሳልጠቀስ የማላልፈው ወቀሳ አለኝ። ይህ ወቀሳየ ደግሞ የኔ ብቻ ሣይሆን የብዙ ጸሐፍት መሆኑን እረዳለሁ። የችግር ትንሽና ትልቅ የለም ብዬ ስለማምን ይህንንም በመጠኑ ማንቀራበጡ አይከፋም ባይ ነኝ - ተገቢ ትኩረት ያልተሰጠው ትንሹ ችግር ነው አድጎ ትልቅ እሚሆን - "እማዬ፣ ምነው በዕንቁላሌ በቀጣሽኝ!" የሚለውን ሥነ ቃላዊ ብሂል እናስታውስ። አንድን ችግር ሳይብስበት መግለጡ ለመፍትሔው በግማሽ እንደመቅረብም ይመስለኛል። ‹ኑ እንዋቀስ‹ አልነበር የሚል ያ አላበሳው ተሰቅሎ የሞተ የዓለም መድሐኒት? ብንዋቀስ ምን ወጪ እናወጣለን? ተዋቅሰን ብንታረቅና የሰይጣንን ቀንድ ብንሰብር ተጠቃሚዎች ነን። ጥቅምን ደግሞ በግድ ከማቴሪያላዊ ጎኑ ብቻ ማየት የለብንም። እንደችግር ሁሉ የጠብም ትንሽና ትልቅ የለውም። ለምሳሌ የኔን ተግባርና ጠባይ ልትንቅ ትችላለህ - እኔን ግን ልትንቀኝ አይገባም። ነውር ነው። ኃጢአትም ነው። እንዳንተው ሰብኣዊ ፍጡር ነኝና አንተ ባንተ ላይ እንዲያደርጉብህ የማትወደውን ነገር ሁሉ በኔ ላይ ልታደርግ አይገባም - ኮንፊውሸስ ተናገረው፣ አሊጋዝ ደገመው እውነቱ ይሄው ነው።

ዝም ብዬ ሳስበው አንዳንድ ድረገፆች ምን እንደሚፈልጉ የሚያውቁ አይመስሉኝም። የሚፈልጉትን ነገር እንዳለማወቅ የመሰለ አስከፊ በሽታ ደግሞ የለም። ጅል ባህል ሆኖባት ሣይሆን አይቀርም ያገሬ ሣዱላ በፍቅር የነሆለለላትን ጉብል ንቃ (ባህሉን ስለሚያውቅ ሆን ብሎ እንድትወደው በማሤር የናቃት መስሎ የሚጀነንባትን ጭምር መሆኑን ልብ ይሏል) የሚንጠባረርባትንና የሚጠላትን እንደምታፈቅር ሁሉ አንዳንድ የድረገፅ አዘጋጆችም በፍቅር የሚንሰፈሰፍላቸውን ወገናቸውን ያለመለየት ችግር አይባቸዋለሁ። በበኩሌ ምን ስጽፍ በየትኞቹ እንደሚወጣና በየትኞቹ እንደማይወጣ አስቀድሜ ዐውቃለሁ - ባብዛኛው። ይህ ዓይነቱ መለስተኛ ልዩነት የሚለመድ ነው - በቂ ምክንያት ኖረውም አልኖረውም በበኩሌ ለምጀዋለሁና አንዳንዶች ነሸጥ አድርጓቸው ፊት ሲነሱኝ ማቅ አልለብስም። ደግሞም - በሚገባ አምናለሁ - የዜጎች ሁሉ አስተሳሰብና አመለካከት በግድ አንድ መሆን የለበትም፤ ልዩነት ይኖራል። ነገር ግን ልዩነት ይኖራል ሲባል በሁሉም ነገሮች በግድ መለያየት አለብን ማለት አይደለም። ልዩነትን ተገድደን የምንቀበለውና ለማጥበብም ከልብ የምንጥርበት ሊሆን ይገባዋል እንጂ በ"ማን ምን ያመጣል?" የፈግጠው ፈግጪው ሁከተኛ መንፈስ አነሳሽነት በቤተ ሙከራ ተፀንሶ የሚወለድና የሚያድግ በጥባጭ "in vitro son" ሊሆን አይገባም። አንድ ሊያደርጉን የሚችሉ ነገሮች መኖር አለባቸው፤ ማወቅ ስለማንፈልግ ይሆናል እንጂ የምንጋራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ተቃዋሚዎችንና ወያኔን አንድ ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮች አይኖሩም ብዬ በበኩሌ አላምንም። በዚህኛውም ሆነ በዚያኛው ጎራ እንደአለመታደል ሆኖ ሁሉንም ነገር የመቃወም ባህል ስላዳበርን እንጂ በምንስማማባቸው ነገሮች እየተስማማን በማንስማማባቸው ነገሮች ብቻ ብንነጋገር ኖሮ ትልቅ ሸክም ከትከሻችን በወረደልን ነበር፤ ግን አንዱ ስንጥቅ ሌላውን ሸለቆ እየፈጠረ ነገረ ሥራችን ሁሉ ባቢሎን ሆኖ ቀረ። ልዩነት ደግሞ በባሕርይው ቶሎ ካላጠበቡትና ከነጭርሱ ካላጠፉት እየተምቦረቀቀ የሚሄድ ክፉ ደዌ ነው። በአሁኑ ሁኔታችን በአንድ ጎራ ውስጥ አሉ በሚባሉ ወገኖች መካከል እንኳን የልዩነት ቀዳዳዎች ሲሰፉ እንጂ ሲጠቡ አይስተዋሉም። ይህም መረገም ነው።

…. ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## በአቶ ሌንጮ ለታ የሚመራው የኦዴግ ልዑካን

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

መንግሥት አቶ ሌንጮ ለታንና የልዑካን ቡድኑን አባላት ከቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት እንደመለሳቸው ሲናፈስ ነበር። ይሁን እንጂ ግንባሩ ባወጣው መግለጫ ከፍተኛ የልዑካን ቡድኑ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ፣ በአዲስ አበባ ቆይታው ከመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በአካል መገናኘት ባለመቻሉ መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ.ም. ወደ ካናዳ መመለሱን ገልጿል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከኦዴግ ጋር እንዲደራደር ለማሳመን ለሁለት ዓመት ግንባሩ ከውጭ በመሆን ጥረት ሲደረግ መቆየቱን፣ በስተመጨረሻም በግንባሩ ውሳኔ ፕሬዚዳንቱ አቶ ሌንጮ ለታ የሚመሩት የልዑካን ቡድን ወደ አዲስ አበባ እንዲጓዝ መደረጉን ይገልጻል። ኦዴግ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በማድረግ የኦሮሞ ሕዝብ መብትና ነፃነት የማስከበር፣ እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲና ብልፅግናን ለማቀዳጀት እንደሚሠራ አስታውቋል።

ይህንንም ዕውን ለማድረግ ከአገር ውጭ ሆኖ ሳይሆን፣ በኦሮሞ ሕዝብ መካከል ሆኖ በሕግ አግባብ ተመዝግቦ ፖለቲካዊ ትግል ለማድረግ መወሰኑን መግለጫው ያስረዳል። በዚህ የግንባሩ መርህ መሠረት መንግሥትንና ሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎችን በተለይም ገዥው ፓርቲን ኢሕአዴግን ወደ ድርድር ለማምጣትና መሠረታዊ ልዩነቶችን ለማስታረቅ፣ እንዲሁም ግንባሩ በኢትዮጵያ መቀመጫውን እንዲያደርግ ሰፊ ጥረት ቢደረግም ሊሳካ አለመቻሉን መግለጫው ያትታል።

“በአዲስ አበባ ከመንግሥት ኃላፊዎች ጋር ተገናኝተን ድርድር አለመጀመራችን ተስፋ የሚያስቆርጠን ሳይሆን፣ ድርጅታችንን በሕዝባችን መካከል ለመመሥረት የምናደርገው ጥረት መጀመርያ ነው።” ይላል መግለጫው።

ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያለውን አቋም በድጋሚ የገለጸው ግንባሩ፣ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ፖለቲካ ተዋናዮች በተለይም ገዥው ፓርቲና ዓለም አቀፍ ደጋፊዎቹ የግንባሩን ጥረት በመልካም ጎኑ እንዲቀበሉ ጥሪ አቅርቧል። ጉዳዩን በተመለከተ የተጠየቁት የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሽመልስ ከማል፣ አቶ ሌንጮና የልዑካን ቡድኑ አዲስ አበባ እንደነበሩ አላውቅም ብለዋል።

## ዘመናዊ ባሪያ ፍንገላ በኢትዮጵያ

... ( ከገጽ 3 የዞረ )

ከዚህ አኳያ የበቀደሙ ጽሑፍ በተለይ የዘወትር ደምበኛው በሆንኩት አንድ ድረገፅ ላይ ሳይወጣ ሲቀር ደንግጫለሁ። በተደጋጋሚ ብጠይቅም እነአያ ሰው ጤፉ ፀጥታን መርጠዋል። የሕዝብ ነፃነት ተሟጋች ማለት እንግዲህ እንዲህ ነው። ውሸታም በሏቸው፤ እኔም ብያለሁ። የአንድን ዜጋህን ጥያቄና ብሶት ለመጋራትና ስሜቱን ለመረዳት፣ ተረድተህም ለማረጋጋት ካልሞከርክ፣ ከዚያም ባለፈ በትዕቢት ተወጥረህ ከተጓደድህበት ውሸታምና የይመስል ታጋይ ነህ - “ፑቲካ!”። አንድ ዜጋ ክቡር ነው። ትግላችንም ለዚያ ነው። እኛ ዘንድ የሌለን መከባበርና መደማመጥ እሌላ ቦታ መፈለግ ላም ባልዋለበት ኩበት ለመልቀም እንደመሞከር ነው።

አንድ ወቅት በጣሊያን ሀገር ለውኃ በተቆፈረ የ36 ሜትር ጥልቀት ጉድጓድ ውስጥ አንድ ሕጻን ይገባና መንደርተኛውና ጠበብቱ ሁሉ እንዴት ሕጻኑን ማውጣት እንደሚቻል በጉድጓዱ ዙሪያ ከብበው ይጨነቃሉ። በዚህ መሀል ወሬውን በተባራሪ የሰማው የሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ይመጣና አብሮ እየተጨነቀና እያዘነ ከሕዝቡ ጋር ሙሾ ያወርድ ገባ። ሰው ማለት እንዲህ ነው፤ መሪ ማለትም። ዜጋቸውን እንደትቢያ የሚቆጥሩ ወያኔዎችን የምንታገለው ሌላ የአፈና ሥርዓት አምሮን ሣይሆን የመሰለንንና የምናምንበትን የኛን እውነት በነፃነት መግለጽ እንድንችል ነው። እርግጥ ነው - አንድ ሰው ወይም አንድ ቡድን የተጻፈው ነገር ትክክል አይደለም ብሎ ሲያምን በዚያው መድረክ በተመሣሣይ መሣሪያ - በብዕር - አጸፋውን በመስጠት የማስተባበልና የማስተማርም ግዴታ አለበት። ከዚያ ውጪ ወደ አፍ እላፊና እጅ እላፊ እንዲሁም ወደመኮራረፍ መሄድ ከሰውነት ደረጃና ክብር መውጣት ነው። ሰዎች ወደነዚህ ጅላጅል አማራጮች የሚዞሩት ትግስት በማጣታቸው ብቻ ሣይሆን የእውነት ስንቅ ስለሚያጥራቸው በካፈርኩ አይመልሰኝ እንደሆነ ግልጽ ነው። አዎ፣ እውነት ስታጥረን ሀሰት ከተፍ ትልና የተጓደለውን ነገር በዛቻም፣ በስድብና በጡንቻም ታሟላልናለች።

የኔን ወረቀት ቦጫጭቆ የጣለው ያ ድረ ገፅ ግን አሁንም ድረስ ግራ እንዳጋባኝ አለ። እንደሰው ድረገፅ ከፍቶ ማስተናገድ ከጀመሩ በኋላ ቀጫጭን ሰበብ እየፈለጉ ተናጋሪን ለማፈን መሞከር ሳቢውን ግረፈው እንዲሉ ነው። ያበጠው ይፈንዳ - ይህ ዓይነቱ አፈና ከወያኔ ያልተናነሰ ብልግና ነው። ያ ጽሐፍ በዚያ ድረገፅ የቅርጫት እራት (በኮምቡጠር ቋንቋ የ“Trash” ቀለብ) ሆኖ ይቀራል ብዬ በእውኔ ቀርቶ በህልሜም አላሰብኩትም። ከናካቴው ያዩትም አልመሰለኝም፤ አይተውት ከሆነና በምንም ምክንት ይን ከተውት ግን በርግጥም የሚዲያ ሥራን አያውቁም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ቆሜያለሁ የሚል “የነፃነት ዐርበኛ” ያን የመሰለ ከመስከረም በሉት፣ ከየካቲትም በሉት(በተወሰነ ደረጃም ቢሆን)፤ ከግንቦትም በሉት ከሌላ ማናቸውም ንቅናቄ ምንም ያህል የጠበቀ ግንኙነት የሌለውን ማኅበራዊ ጉዳይ ገሸሽ ሲያደርገው “የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” የሚለውን ክርስቶሳዊ ተማጽኖ ከማስታወስ ውጪ ሌላ ቃልም ሆነ አስተያየት የለኝም። የሚዲያ ሥራ ሆደሰፊነትን፣ ዕውቀትና ችሎታን፣ ሃቀኝነትን፣ አለማድላትን፣ አለማግለልን። ሙያዊ ትምህርትና ሥልጠናን፣ በጥቅም አለመደለልን ... ይፈልጋል፤ ፈራጅና ዳኛው አንባቢ ወይም አድማጭና ተመልካች እንጂ እሱ የመረጠለትን ብቻ የሚያሣልፍ ከሆነ መጥፎ አሣላፊ ሆነ ማለት ነው። ጋዜጠኛ በሁለት የተራራቁ ጫፎች መሀል የተቀመጠ የሁለቱም ጫፎች የወል አገልጋይ እንጂ ከሁለቱ ወደ አንድኛው የሚሳብ ሊሆን አይገባም - ሰው ነውና አይሳብ አልልም፤ በሥራው ላይ እስካለ ግን አንዱን በመውደድ ሌላውን በመጥላት ሚዛኑን የሚስት ከሆነ የፓርቲ/የድርጅት ልሣን እንጂ የጋዜጠኝነት ሙያዊ ሥነ ምግባር የሚፈቅደው አሠራር አልተከተለም - ኅሊናውንም አቆሸሸ። ከዚህ መሠራተዊ መርህ አኳያ ድረገፆቻችን ቢፈተሹ ... ለነገሩ ማነው ወንዱ ለመፈተሽ የሚነሣ! ማንስ ሊሰማው። ለማንኛውም ማንም ደመ ሞቃት ካለበቂ ሙያዊ ዕውቀትና ግንዛቤ ከሜዳ እየተነሣ ጋዜጠኛ ልሁን ቢል ኢቲቪን ከሚያስታውሰን በስተቀር ሊታይና ሊጨበጥ የሚችል የረባ ሥራ አይሠራም። ዐርፎ እቤቱ ቢቀመጥ ወይም ሌላ ነገር ቢሠራ ነው የሚሻለው። ከልብ ነው ያዘንኩት። ሰው ደግሞ በወደደው ያዝናል። አለበለዚያማ ስንትና ስንት ሺህ ድረገፅ ሞልቶ የለም እንዴ? ደግሞ ለድረገፅ! የኮምፒውተር እናት በድባብ ትሂድ። እኔም እዚህ ሀገር ውስጥ ቀረቀር ውስጥ አጓጉሊት ተሰንቅሬ ባልገኝ ኖሮ አሥሩን ከፍቼ አራውጠው ነበር።(ብዙ ጊዜ የሚያሣዝነኝ ነገር - ብዙ ነገሮች ወደኢትዮጵያ ሲገቡ ተፈጥሯቸውን ይለውጡና amorphous ይሆናሉ - ቅርጽ አልባ። ጥሎብን ፖለቲካችንም ሽፋፋ፣ ንግዳችንም ሽፋፋ፣ ዕድገታችንም ኳሻርኳራዊ ምች ያጠናገረው ግንጥል ጌጥ፣ የትምህርት ሥርዓቱ ሽፋፋ፣ መንግሥታዊ ተቋማችን ሽፋፋ፣ የግብርና የቀረጥ አተማመን ደንባችን ሽውራራ፣ መሪዎቻችን የአእምሮ መካኖች፣ አንዳችን ለአንዳችን ያለን አመለካከት ሽፋፋ፣... በአሁኑ ወቅት ምን ያልተንሻፈፈ ነገር አለን? በመጪው ዘመን ስንቱን ሽፋፋ አቃንተን እንደምንዘልቀው ፈጣሪ ይወቅ።)

### ወደ ጥንተ ነገራችን እንመለስ።

ባጭር ባጭሩ ልንገራችሁ። ዘመናዊ ባርነት በኢትዮጵያ ነግሦኣል። እንዲህ ስላችሁ ባለፈው ጦማሬ እንደገለጸኩት ብዙዎቻችን የምንጠበስበትን የኑሮ ውጣ ውረድና የፖለቲካ እመቃ ማለቴ አይደለም። ከዚያም የከፋ የለዬለት ዘመናዊ ባርነት አለላችሁ።(በነገራችን ላይ ባለፈው ጽሑፌ የአንድ ኪሎ ብርቱካን ዋጋ 22 ብር ገደማ ያልኳችሁ በጣም ተሳስቻለሁ - 45 ብር ገብቷል አሉ፤ ልብ አድርግ የአንድ ኪሎ ብርቱካን በችርቻሮ የመሸጫ ዋጋ 45 ብር ብቻ! ጉድ በል ጎንደር ማለት አሁን ነው።)

ሚሚ ስባሃቱን የማያውቅ መቼም አይኖርም። የማታውቋት ካላችሁ - በቪኦኤ የአማርኛው ክፍል ትሠራ የነበረች፤ ከዚያ ተባርራ ይሁን በራሷ ፈቃድ ወጥታ ወደኢትዮጵያ የገባችና በርሷና በባሏ ስም የመነሻ ፊደላት “ዛሚ” ተብሎ በሚጠራ የኤፍኤም ሬዲዮ ጣቢያ በአብዛኛው ወያኔን እያገለገለች የምትገኝ “ጋዜጠኛ” ናት - አንዳንድ ማኅበራዊ ችግሮችን ማንሳቷንም አልክድም፤ ይህንን በጎ ሥራዋን በአወንታዊነት አደንቃለሁ። ... አዜብ መስፍን የምትባለዋን ጉድ ደግሞ የማያውቅ ይኖራል ብዬ አልገምትም። እንደድንገት የማያውቅ ቢኖር አዜብ መስፍን ወይም አዜብ ጎላ ማለት የቀድሞውንና የዐፅመ-ዕድሜ ልክ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ጨምሮ የብዙዎች ሚስት እንደነበረችና እንደሆነች በብዛት የምትታማና - የአሁን ሁኔታዋን እንጃላት እንጂ - ወንዶችን ብቻ ሣይሆን ንግዱንና የንግዱን ማኅበረሰብ በሞላ እንደፈለገች የምታተረማምስ ሦስተኛዋ ዮዲት ጉዲት እንደሆነች የሚነገርላት ልዩ እስፊንክስ (Sphinx) ናት - ወደመጀመሪያዋ ዮዲት መሄድ ሳያስፈልገን ከሌላኛዋ መበለት ከገነት ዘውዴ ቀጥላ መሆኑ ነው ሦስተኝነቷ፤ ( እንዳለመታደል ሆኖብኝ አንዳንዴ ፈታ ብሎ መናገር ደስ ስለሚለኝ እንጂ ስለዚች ሴትዮ የግል ጠባይ እዚህ መናገሬ ስህተት መሆኑን ዐውቃለሁ፤ ሂሴን ውጫለሁ።) እነዚህ ሁለቱ አዜብና ሚሚ የሚሰኙ ጉዶችና ሌሎች እነሱን የተከተሉ ጥቂት የማይባሉ ባሪያ ፈንጋዮች በሀገራችን የሚሠሩት ተዓምር ልዩ ነው። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የዛሬ አሥራ ሦስት ዓመት ገደማ በአንድ ታዋቂ የግል ጋዜጣ አንድ መጣጥፍ ማውጣቴ ትዝ ይለኛል - ሰሚ ግን አልተገኘም። መጯጯኽ እንጂ መደማመጥ ብሎ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ጭራሽ የለም። ( **ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል**)

**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org